የነገረ አበው (Patrology) ትምህርት መግቢያ

ለግቢ ጉባኤያት ተተኪ መምህራን
ማሠልጠኛ የተዘጋጀ

ግንቦት 2008 ዓ.ም

መግቢያ

- የክርስትና ሃይማኖት ከእግዚአብሔር የተሠጠች መገለጥ ናት። (ይሁዳ.፩÷፪)
- ቀድሞ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያቀደውን ድኅነት እና ሊገልጠው ያሰበውን ምስጢር በነቢያት አመልክቷል።
- በኋላ የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ፍጹም ሰው በመሆን ለሰው ልጅ የሚያስፈልገውን ምስጢር ገለጠ፤ ድኅነትን ፈጸመ። (ዕብ. ፩÷፩)
- የድኅነቱን የምሥራች (ወንጌልን) ይሰብኩ ዘንድም ከዋለበት እያዋለ ካደረበት እያሳደረ ያስተማራቸውን እና የሥራው ሁሉ የዓይን ምሥክሮች የሆኑትን ሐዋርያትን ወደ አለም ሁሉ ላከ።
- ከዚያም በኋላ በእነርሱ የተተኩ እና ትምህርታቸውን ጠብቀው ሳይበርዙ ሳይከልሱ ለትውልድ ያስተላለፉ አባቶች በየዘመናቱ አልፈዋል።

- እንግዲህ የቀድሞዎቹ ነቢያት፣ ቀጥሎም ሐዋርያት በኋላም በነርሱ የተተኩ ሊቃውንት ሁሉ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ይባላሉ።
- በዚህ ጽሑፍ ግን የምናተኩረው ከሐዋርያት በኋላ ስለተነሱት የቤተክርስቲያን ሊቃውንት አባቶች ነው።
- ይህ ከሐዋርያት በኋላ የተነሱ እና በጽሑፍ እና በቃል የተሠጣቸውን ታላቁን ሐዋርያዊ ትውፊት (Apostolic Tradition) ጠብቀው እና ከመናፍቃን እየተከላከሉ ያስተላለፉ፣ መጻሕፍትን የተረጎሙ፣ ድርሳናትን የደረሱ በአጠቃላይ በሕይዎታቸውም በትምህርታቸውም ቤተ ክርስቲያን የመሠከረችላቸው አበው የሚወሱበት ትምህርት “ነገረ አበው (Patrology)” ይባላል።

ነገረ-አበውን ማጥናት ለምን ይጠቅማል?

- ቤተ ክርስቲያን ትምህርቷን እና ሕይወቷን ከትውልድ ወደ ትውልድ የምታስተላልፍበት ሕያው መንገዷ በየዘመኑ የሚነሱ በሕይዎታቸውም በትምህርታቸውም የወንጌልን ሕይወት የኖሩ እና ሌሎችም ይቀበሉት ዘንድ ባስተማሩ ቅዱሳን ነው።
- የቤተ ክርስቲያን ትምህርቷ እና ሕይወቷ በቅድስና በኖሩ እና የመጻሕፍትን ምሥጢር በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በተረዱ ቅዱሳን ሰዎች በኩል ለትውልድ የሚስተላለፍ እንጂ በቅዱሳት መጻሕፍት ንባብ ብቻ የሚስተላለፍ አይደለም።
- ነገረ አበው ሕይወታቸው ከትምህርታቸው ትምህርታቸው ከሕይወታቸው ጋር የተስማማ ቅዱሳን አበው ሕይወታቸው እና ትምህርታቸው የሚጠናበት ትምህርት ነው።
- በቤተ ክርስቲያን መልካም የቅድስና ኑሮን የኖሩ እና ርቱዕ ሃይማኖትን ሳይበርዙ ሳይከልሱ ያስተማሩ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በገለጠላቸው መጠን እንደየዘመኑ ሁኔታ ያብራሩ እና የተረጎሙ አበው እጅግ ብዙዎች ናቸው።
- እግዚአብሔር በየዘመኑ እንዲህ አይነት ሰዎችን ለቤተ ክርስቲያን አላሰጠምም።

የነገረ አበው አስፈላጊነት

- ነገረ አበው አንዱ የነገረ መለኮት ክፍል ሆኖ ብቻውን የሚጠና አይደለም። ለሁሉም የነገረ መለኮት ትምህርት ዘርፎች መሠረታዊ ትምህርት ስለሆነ ጥቅሙን መወሰን አይቻልም።

2.1 ቅዱሳት መጻሕፍትን በትክክል ለመረዳት፦

- መጽሐፍ ቅዱስ (አሥራው መጻሕፍት) ግንዘብነቱ የቤተክርስቲየን መሆኑ የሚታወቅ ነው። በመሆኑም ቤተክርስቲያን ከእግዚአብሔር በተቀበለችው መንፈሳዊ ሕይወቷ መጽሐፍ ቅዱስን ትተረጉማለች።
- የመጽሐፍ ቅዱስ መሰጠት ዓላማወውንና በውስጡ የያዛቸው የተለያዩ የነቢያትና የሐዋርያት መጽሐፍት የሃሳብ ስምምነት በአበው አንደበት ታስተምራለች። ብዙዎች አባቶች መጽሐፍ ቅዱስን በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት መተርጎመቻው ለነገረ አበው ትምህርት ትልቅ መነሻ ነው።
- መጽሐፍ ቅዱስ ማለት የማይወሰነው የእግዚአብሔር ሃሳብ በሚወሰን የሰው ቋንቋ የተጻፈ ማለት ሲሆን በየዘመናቱ የተነሱ አበው ይህን በመረዳት የመጽሐፍ ቅዱስን የተለያዩ ቃላትና ታሪኮችን በብዙ ጎብረ መልክዕ በመመልከት ተርጉመዋል። የጻፉዋቸው ትርጓሜያት የአባቶችን አስተሳብና አስተምህሮ ለመረዳት የሚያስችሉ ናቸው።
- በሌላ አገላለጽ ነገረ አበውን ማጥናት ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ያለውን ኦርቶዶክሳዊ መረዳትን ያስገኛል።

2.2 ነገረ ቤተክርስቲያንን ለመረዳት፡-

- የአበው ትምህርት ቤተክርስቲያን በምድር ያለች የእግዚአብሔር መንግስት መሆኗን ያስገነዝባል። ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ደም የተቀደሰች በመሆኗ ሁልጊዜ ወደ ረ኷ ክርስቶስ መሄድን ትናፍቃለች። ለዚህም በምድር ሳለች ለአእምሮ የሚመች እውነተኛ ክብር ለእግዚአብሔር የምትሰጥ÷ ስለ ፍጥረትም ሁሉ ሃላፊነት ወስዳ የምትማልድ ÷ስለ ሰው ሁሉ መዳን የምትጸልይ÷የምትጋደል የክርስቶስ አካል መሆኗን በተረዳ የምናውቀው በነገረ አበው ትምህርት ነው።
- አበው እንደ ግሪኩ ፍልስፍና ያይደለ ከክርስቶስ እንደተቀበሉት ትምህርታቸው ግዙፉን ዓለም ከረቂቁ÷ፍጥረትን ከፈጣሪው አንድ የሚያደርግ ነው።
- ይኸውም ቤተክርስቲያን የህልውናዋ መሠረት የሆነው መስዋዕቷ ጎበስትና ወይን የሚታይ የሚዳሰስ ሆኖ ጊዚያዊ ሕይወቷን ለእግዚአብሔር ታቀርባለች፤ እርሱም የክርስቶስ ሥጋና ደም አድርጎ ዘላለማዊ ሕይወት በማድረግ ይሰጣታል።
- እንዲህ ባለ ስስት በሌለበት ፍቅር ሰው ከአማላኩ ጋር ይኖር ዘንድ አበው በቃልም በተግባርም አስተምረዋል።

2.3 <u>የቤተክርስቲያን ታሪክ ለመረዳት</u>፡-

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ አምላክ ሲሆን ስለ ሰው ልጅ ብሎ በዘመንና በቦታ ተወስኖ ሰው ሆኖ የተገለጠ እንደሆነ ሁሉ አካሉ የሆነች ቤተክርቲያን በጸጋ እግዚአብሔር ከዘመንና ከቦታ በላይ ሆና ዘላለማዊ ብትሆንም በዚህ ዓለም የምትገኝ የእርሱ መንግስት ናትና ታሪክ አላት።
- የዚህችን ቤተክርስቲያን ታሪክ ያለ አባቶች ለማወቅ መሞከር ከቶ አይቻልም።
- የክርስቶስ ሪድኤት የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የተገለጠባቸው ካለእነርሱ የቤተክርስቲያንን ማንነትና ታሪክ መረዳት አይቻለም።
- ቤተክርስቲያን ማኅበርና መንፈሳዊት አንድነት ተብላ መጠራቷ በእነርሱ ነውና። የእነርሱ ሕይወታቸው÷ ተጋድሎአቸው÷ ትምህርታቸው÷ ከመናፍቃን ጋር ተከራክረው መንጋውን መጠበቃቸው የቤተክርስቲያን ታሪክ አካል ነው።
- ታሪኳን ለመመዝገብ ቤተክርስቲያን ብዙም የተጨነቀች ባትመስልም አውሳብዮስ ዘቂሣሪያን የመሰሉ አንጻራዊነት አተያይ ትክክለኛውን የቤተክርስቲያን ታሪክ የመዘገቡ ሰዎች ነበሩ።

2.4 <u>የክርስቲያናዊ ኑሮን ለመረዳት</u>፡-

- በሰው በደል ምክንያት «እሾህና አሜኬላ ይ ብቀልብሽ» ዘፍ. 3 በተባለች ምድር ላይ ሰው እየኖረ እሾሁ አይውጋኝ ማለት አይችልም።
- ሰውን ለማዳን ክርስቶስ ሲመጣ ምንም ንፁሐ ባህርይ አምላክ ቢሆን በፈቃዱ የሰውን ድካም እና ሕማም ገንዘቡ አድርጓል÷ ደክሟል÷ ተርቧል÷ ተጠምቷል÷ በሥጋ ቆስሎ በነፍስ አዝኗል÷ ተክዟል፤ ይህን ሁሉ ተቀብሎ÷ ይህን ሁሉ ባርኮ ለክርስቲያኖች ሰጥቷል። መስቀሉንተሸክመውእንዲከተሉአዟል።
- ይህን ሁሉ ድካም ወደ ኃይል÷ ሞትን ወደ ሕይወት ለውጦ በግብር እንድንመስለው አርዓያ ሆኖናል።
- ይህን በክርስቶስ የሆነውን ሕይወት መማሪያ ሰሌዳዎቻችን አባቶች ናቸው።
- ነገረ አበው የአበውን ትምህርትና አስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን የደረሰባቸውን እንግልት ÷ስደት ÷እስራት ይህን ሁሉ ስለሃይማኖት በአኮቴት (በምስጋና) መቀበላቸውንያስተምረናል።

2.5 ነገረ ማርያምን በትክክል ለመረዳት፡-

- ንጽሕት ሆና ብትገኝ እግዚአብሔር ሰው ይሆንባት ዘንድ የወደዳት እመቤታችን ለኦርቶዶክሳዊው ሥርዓተ አምልኮ ሕይወት ናት።
- ንፁህ አምላክን የተቀበልንባት ንጽሕት እጅ ድንግል ማርያም ናት።
- ኦርቶዶክሳውያን አባቶች አምላክ ሰው የመሆኑን ነገር ሲያስተምሩ እሷን ሳያነሱ÷ ለሰው መመኪያ መሆኑዋን ሳይመሰክሩ የማይቻል ነው።
- በተለይም እነ ቅዱስ አግናጥዮስ÷ ቅ/ሄሬኔዎስ÷ ሰማዕቱ ዮስጢኖስ÷ ቅዱስ ኤፍሬም÷ ቅዱስ ያሬድና አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በስፋት ስለክብሯ ÷ስለንጽሕናዋ በሰው ድኅነት ላይ ስላላት ድርሻ በቤተክርስቲያን ያላትን ቦታ በስፋት ማስተማራቸው አሁን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጀመረ ልል ትምህርት እንዳይደለ ያስረዳል።
- ይልቁንም ከሐዋርያት ጀምሮ የጸና ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ መሆኑን ለመገንዘብ ነገረ አበው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ምዕራፍ 3

የቤተክርስቲያንአባቶች

- ኦርቶዶክሳዊውን አስተምህሮ በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር ያስተማሩትን በትምሕርታቸውም መንፈሳዊ ልጆችን የወለዱትን የቤተክርስቲያን መምህራን የቤተክርስቲያን አባቶች እንላቸዋለን።
- «አባት» የሚለው መጠሪያ በጳጳሳትና በቀሳውስት ብቻ ሳይወሰን በኦርቶዶክሳዊ ጽሑፎቻቸው ሃይማኖት እንዲጸና ምግባር እንዲቃና ያደረጉ ኦርቶዶክሳወውያን መምህራንን ያጠቃልላል። ቅዱሳት መጻህፍት እንደመሰከሩት አምልኮተ እግዚአብሄርን ይዘው ሌላውም በዚህ እንዲኖር ያደረጉ እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ያልተለያቸው አብርሃም÷ይስሐቅና ያዕቆብ «አባቶች» በመባል ይታሰባሉ። (የሐዋ.ሥራ 3÷13)
- በነገረ አበው ሊቃውንት ዘንድ አንድን የቤተክርስቲያን መምህር የአባትነት ዕውቅና ለመስጠት አራት መስፈርቶች አሉ።
- ሀ. <u>ድርሳናትን የጻፈ</u>፡- ቤተክርስቲያን በተለያዩ ዘመናት ያጋጠሟትን እንግዳ ትምህርቶችን ተቃውሞ ወይም ክርስቲያኖች የቤተክርስቲያንን ትምህርት እንዲረዱ ጽሑፎችን የጻፈ።

- ለ. <u>ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ</u>፡- በመገለጥ የተገኘውን አምላካዊ ምስጢር ቤተክርስቲያን እንደተረከበችው እርሱም በትምህርቱ ለሌላው ያስረከበ።
- ሐ. <u>የሕይወት ቅድስና</u>፡- ኦርቶዶክሳዊውን አስተምህሮ ከሕይወት ነጥሎ ማየት አይቻልም። ስለሆነም ኦርቶዶክሳዊውን አስተምህሮ በጽሑፎቹ በማንጸባረቅ ያስተማረው መምህር የሕይወቱ ቅድስና የቤተክርስቲያንን ማንነት የሚገልጽ ነውና የሕይወት ቅድስና ለአባትነት አንዱ መስፈርት ነው።
- መ. <u>ቀደምትነት</u>፡- ይህን መስፈርት በተመለከተ የነገረ አበው ሊቃውንት የተለያዩ አስተያየቶችን ይሰጡበታል። ይህም ቀደምትነት እስከ መቼ ያለውን እንደሆነ ማለታችን ነው። አንዳንድ ሊቃውን እስከ ጉባኤ ኬልቄዶን ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ የደማስቆው ቅዱስ ዮሐንስ እስከተነሳበት እስከ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ነው የሚሉም አሉ።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የ**ነገረ አበው ቦታ**

- ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርነው ነገረ አበው የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ከነሱ በፊት ከተነሱ መምህራን በትክክል ተረድተው በኑሮአቸው የተረጎሙ እና ያስተማሩ አበው ሕይወታቸው እና ትምህርታቸው የሚጠናበት ነው።
- ነገረ አበው እንደ አንድ የነገረ መለኮት ትምህርት ክፍል የሚጠና ብቻ ሳይሆን ሁሉንም የነገረ መለኮት ትምህርት ዘርፎች የሚነካ ነው።
- የኦርቶዶክሳዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አስተምሮዋ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የተመሠረተ (Scriptural) እና በቅዱሳን ሊቃውንት የተተረጎመ (Patristic) ነው።
- በእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን የታሪክ ጉዞ ውስጥ የቅዱሳን አበው ተጋድሎ እና በቃልና በጽሑፍ ጥለው ያለፉት አሻራቸው ሲወሳ ይኖራል።
- በዚህ ርእስ በተለያዩ የታሪክ ዘመናት የቅዱሳን አበው አስተዋጽኦ ምን እንደነበረ አጭር ዳሰሳ እናደርጋለን።

ሀ. ነገረ አበው በመጀመሪያዎቹ መቶ ክፍለ ዘመናት

- በመጀመሪያዎቹ መቶ ክፍለ ዘመናት (እስከ ኬልቄዶን ጉባኤ ድረስ) እስካሆን ድረስ ትምህርታቸው ቤተ ክርስቲያንን የሚጠብቅ እነ ቅዱስ አግናጤዎስ (ምጥው ለአንበሳ)፣ ቅዱስ አቡሊናርዮስ ዘሮም፣ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን የመሳሰሉ ከዋክብት ሊቃውንት የተነሱበት ዘመን ስለሆነ በነገረ አበው የቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመን ይባላል።
- የነዚህን ዘመናት የአበው ትምህርቶች በሦስት ዘርፎች መመልከት እንችላለን።

1. ሥርዓተ-ቤተ ክርስቲያንን

- ምንም እንኳ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ምንጩ እና መሠረቱ የብሉይ እና የሐዲስ መጻሕፍት እና የሐዋርያት ትውፊት ቢሆንም ይህን አስፋፍተው እና ምሥጢሩን አደላድለው ያስቀመጡ ግን ጥንታውያን ሊቃውንት ናቸው።
- በዚህም እነ ቅዱስ አቡሊናርዮስ ዘሮም፣ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ፣ ቅዱስ ያዕቆብ ዘኢየሩሳሌም ተጠቃሾች ናቸው።
- ከዚህም በተጨማሪ በየጉባኤያቱ የተወሰኑት የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ቀኖናዎች በመንፈስ ቅዱስ የተቃኙ ሊቃውንት አበው አሻራ ያለባቸው ናቸው።

2. ጥብቅና (Apologetics)

- በታሪክ እንደሚታወቀው እነዚህ ዘመናት መናፍቃን በአንድ በኩል ከኢ-አማናያን ፈላስፎች በሌላ በኩል ደግሞ እንደገና ወደ ኦሪት መመለስ በሚፈልጉ አይሁድ ዘመሞች (Judizers) ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን እጅጉን የተፈተነችበት ዘመን ነበር።
- ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ርቱዕ አስተምህሮዋን ጠብቃ እነዚህን ዘመናት ያለፈችው በመንፈስ ቅዱስ ጥበብ በበረቱ በቅዱሳን ሊቃውንቷ ተጋድሎ ነው።
- ለነዚህ መናፍቃን መልስ ለመስጠት እና ለቤተ ክርስቲያን ርትዕት አስተምህሮ ጠበቃ ለመሆን ዘመናትን የሚሻገሩ አያሌ መጻሕፍትን ጽፈዋል።
- በዚህ የጥብቅና ሥራ አዝተው ከደከሙ አበው መካከል ቅዱስ ዮስጢኖስ ሰማዕት፣ ቅዱስ ሄሬኒዮስ ዘልዮን፣ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፣ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ እና ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ተጠቃሾች ናቸው።

3. የመጻሕፍት ትርጓሜ

- ከላይ የዳሰስናቸው የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እና የጥብቅና ሥራዎች በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው እና የአብዛኛዎቹ ምንፍቅናዎች ምንጭ መጻሕፍትን በቤተ ክርስቲያን መንፈስ ሳይሆን በራስ መረዳት ብቻ ለመተርጎም ሲሞከር በሚመጣ ስህተት በመሆኑ ሊቃውንት አባቶች የመናፍቃንን ስህተት ለመግለጥ የመጻሕፍትን ትርጓሜ እያቃኑ ተርጉመዋል።
- ነገር ግን በተለየ ሁኔታ ወጥ ለሆነ የመጻሕፍት ትርጓሜ (Exegesis) ትኩረት ሰጥተው የሠሩ አባቶች አሉ።
- ከነዚህ መካከል ታላቁ መተርጉም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፣ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ ተጠቃሾች ናቸው።
- ለማጠቃለል ያህል የመጀመሪያዎቹ መቶ ክፍለ ዘመናት ጽሑፎቻቸው ዘመናትን አቋርጠው ለትውልድ የተላለፉ ታላላቅ ሊቃውንት የታዩበት ወርቃማ የቤተ ክርስቲያን አበው ዘመን ነበር።

ለ. ነገረ አበው በመካከለኛ እና በቅርብ ዘመናት

- አንዳንድ የነገረ አበው አጥኚዎች ዘመነ አበውን (Patristic Era) እስከ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ይገድቡታል። ለዚህም ምክንያታቸው ቤተ ክርስቲያን “ሳትከፋፈል” የኖረችው በነዚህ ዘመናት ስለሆነ ከዚያ በኋላ አካባቢያዊ እንጂ አለማቀፍ እውቅና ያላቸው አበው አልተነሱም፤ ቢነሱም የቀድሞዎቹ አበው ካቆዩት በላይ ብዙም ያስፋፉት ነገር የለም የሚል ነው።
- ሌሎቹ ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ ለሚያሠራው ሥራ ዘመን እንደማይገድበው ሁሉ ሊቃውንት አበውም በየዘመኑ ሊነሡ ይችላሉ፤ ዘመናት ለሚያመጡአቸው እንግዳ አስተሳሰቦች እና ፈተናዎች ከቤተ ክርስቲያን ርቱዕ አስተምህሮ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መፍትሔ የሚሰጡ እና ይህንንም ለትውልድ የሚያስተላልፉ አባቶች ሲገኙ እንደጥንታውያኑ ተቆጥረው ሊጠኑ ይገባል ይላሉ።
- በተለይ እንደ ቅዱስ ያሬድና አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ያሉ ታላላቅ ሊቃውንት ከኬልቄዶን ጉባዔ በኋላ ለተገኙባት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን “አበውን ዘመን አይገድባቸውም” የሚለው ትንታኔ ተስማሚ ነው።

- ከስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ የተነሱ አበው ከፊተኞቹ አንጻር ብዙዎች አይደሉም። በአለም አብያተ ክርስቲያናት በጎላ የሚታወቁት የኬልቄዶንን ጉባዔ በመቃወም ለተዋሕዶ ጥብቅና የቆሙት ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ፣ ቅዱስ ያዕቆብ ዘእልበረዴ፣ ቅዱስ ፊሊክሲኖስ እና ደቀ መዛሙርቶቻቸው ናቸው።
- በኢትዮጵያ ደግሞ ብዙ ሊቃውንት አበው ያለፉ ሲሆን ከላይ እንደጠቀስነው በቅድስናቸው የተመሰከረላቸው እና በመጽሐፍቶቻቸው ድርሰቶቻቸው እና ትምህርቶቻቸው ትውልድ የተሻገሩ እነ ቅዱስ ያሬድና አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ተጠቃሾች ናቸው።
- በቅርብም የታዩ እነ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬን የመሳሰሉ ሊቃውንት የጥንት አበውን ፈለግ የተከተሉ ናቸው።

የቤተ ክርስቲያን አባቶችን መጻሕፍት ለመረዳት የሚያስፈልጉን ነገሮች

- ማንኛውም የቤተ ክርስቲያንን ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ ከነሙሉ ሕይወቱ እና መንፈሱ መረዳት የሚፈልግ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትነት የአበውን መጻሕፍት በጥንቃቄ ማንበብ እና መረዳት አለበት።
- ይህን ማድረግ የሚችለውም የሚከተሉትን ነገሮች ሲጠብቅ ነው።

፩. የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በአንድ አባት ጽሑፍ ላይ ብቻ መወሰን አይገባም።

- ታላቁ የቤተ ክርስቲያን ትውፊት መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርገው ብዙ አባቶች የተረጎሙት እንጂ በአንድ አባት ትምህርት ብቻ የተብራራ አይደለም። ስለዚህ በአንድ ርእሰ ጉዳይ ላይ በቂ እውቀት ለማግኘት በርከት ያሉ የአበው መጻሕፍትን መመርመር ይገባል።

፪. ከአንድ አባት የመጽሐፍ ገጾች ከመጥቀሳችን በፊት መጻሕፍቱን አንብበን የዚህን አባት ጠቅላላ እሳቤዎች ማጥናት አለብን።

- በዚህ መሰረት ካልሆነ ግን ያላገባቡ (without context) ጠቅሰን እኛ ተሳስተን ሰውን ልናሳስት እናችላለን።

፫. ብዙዎቹ አባቶች በዘመኑ የነበሩ ፍልስፍናዎችን የተማሩ ስለነበሩ ለዘመናቸው ሰው ለማብራራት የዘመኑን የፍልስፍና ቃላት () በጽሑፎቻቸው ውስጥ ተጠቅመዋል።

- ስለዚህ ያለፉበትን የፍልስፍና ታሪክ እና የዘመናቸውን የዕውቀት ክበብ ማጥናት መጻሕፍቶቻቸውን ያለ ጉድለት ለመተርጎምና ለመረዳት ጠቃሚ ነው። ባጠቃለይ ያስተማሩት በዋነኝነት ለዘመናቸው ትውልድ ስለሆነ የኖሩበትን ትውልድ ሁኔታ፣ ቋንቋውን፣ አስተሳሰቡን፣ አኗኗሩን፣ እና ባሕሉን ማወቅ ትምህርታቸውን በደንብ እንድንረዳ ይጠቅመናል።

፬. መንፈሳዊ ትምህርትን ለመማር ከሰው ልቡና በተጨማሪ የመንፈስ ቅዱስ ብርሃን ያስፈልጋል።

- የአበውንም መጻሕፍት ለመረዳት በነርሱ አድሮ ያጻፈ የእግዚአብሔር ኃይል ለኛም ይገልጥልን ዘንድ በቅን ልቡና መጸለይ ይገባል። “አንድ ሰው የነገረ መለኮት ሊቅ መሆን የሚችለው የጸሎት ሰው ከሆነ ብቻ ነው” እንዳለ አንድ ሊቅ።

የቅዱሳን አበው ትምህርት ዳሰሳ (በጥቂቱ ለማሳያነት ብቻ)

- የቅዱሳን አበውን ጽሑፎች በዚህ አጭር ጽሑፍ ማጠቃለል የማይታሰብ ነው። ነገር ግን እንደ ማሳያ የሚሆኑ የጥቂት አባቶችን ሕይወትና የአስተምህሮዎቻቸውን ትንሽ ቅምሻ ከዚህ በታች እናቀርባለን።

የቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ሕይወቱ እና ትምህርቱ

አጭር ዳሰሳ

- የቅዱስ አትናቴዎስ ዜና ሕይወት

- ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ በ298 ዓ.ም በእስክንድርያ ተወለደ።
- ቅዱስ አትናቴዎስ በህጻንነቱ በጨዋታ ሜዳ ከህጻናት ጋር እርሱ አጥማቂ እነርሱ ተጠማቂ እየሆኑ ሲጫዎቱ ፓትርያርክ እለእስክንድሮስ አይቶ ወደ መንበረ ፕትርክናው በመውሰድ እንዳሳደገው ሩፊኖስ የተባለው የዚያን ዘመን ታሪክ ጸሐፊ ዘግቧል።
- እለእስክንድሮስ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት እና ሥርዓት እንዲሁም ሌሎችን የዘመኑ ዕውቀቶች እያስተማረ ካሳደገው በኋላ ለመዓርገ ምንኩስና በቃ።
- በቅድስናው፣ በሞያውና በግብረ ገብነቱ እንከን የሌለው ወጣቱ አትናቴዎስ በ23 ዓመቱ ሊቀ ዲያቆን ሆነ።

- በዚያ ዘመኑ መዓርግ “ሊቀ ዲያቆን” ማለት የሊቀ ጳጳሱ አፈ ጉባኤ፣ እንደራሴ እንደ ማለት ነበር። (የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣ አባ ጎርጎርዮስ (ጳጳስ)፣ 1978 ዓ.ም.፣ ገጽ 94)
- በአጠቃላይ የአራተኛው መቶ ዓመት የቤተ ክርስቲያን ተጋድሎ ከአርዮሳውያን እና ተረፈ አርዮሳውያን ጋር የተደረገ እንደነበረ ታሪክ ይነግረናል።
- ቅዱስ አትናቴዎስንም ጎልቶ እንዲወጣ እና ታላቅነቱ እንዲታወቅ ያደረጉት በዚሁ ዘመን የነበረው የአርዮሳውያንና ተባባሪዎቻቸው ሁከትና ሴራ ነው።
- አርዮስ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ላይ የክህነት ኃላፊነት ተሰጥቶት ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲያስተምር ተሹሞ የነበረ ሊቢያዊ ቄስ ነበር።
- በኋላ ግን “ወልድ በመለኮቱ ፍጡር ነው” የሚል ትምህርት እያስተማረ እና የቅዱሳት መጻሕፍትን ንባባት ለዚሁ ትምህርቱ በሚረዳው መልኩ እየተረጎመ ምንፍቅናውን በታላቅ ትጋት በማስተማሩ እርሱ እና መሰሎቹ ቤተ ክርስቲያንን ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ አውከዋታል።

- በዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያውን ዓለም አቀፍ ጉባኤ አድርጋለች።
- ይህ ጉባኤ በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ አስተባባሪነት እና በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ በእለእስክንድሮስ መሪነት በ 325 ዓ.ም በኒቅያ (አሁን ቱርክ ውስጥ ባለች ቦታ) ተካሄደ።
- በጉባኤው 318 ጳጳሳት ብዛት ካላቸው ቀሳውስት እና ዲያቆናት ጋር ተገኝተዋል።
- በጉባኤው የአርዮስን ምንፍቅና በማጋለጥ እና ትክክለኛውን የቤተ ክርስቲያን ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት በሚገባ ከገለጡ ሊቃውንት መካከል ለጊዜው በሊቀ ዲያቆንነት እለእስክንድሮስን ተከትሎ የሄደው በኋላ እለእስክንድሮስ ሲያርፍ በእስክንድርያ መንበር በሊቀ ጳጳስነት የተሾመው ቅዱስ አትናቴዎስ ዋናው ነበር።
- በተለይ አርዮስን በጉባኤው ፊት ተከራክሮ በመርታቱ እና አርዮሳውያን መሠረቱን ሊንዱት የጣሩትን የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ትምህርት በጽሑፍና በቃል በማስተማር በማስጠበቅ ኃላፊነቱን በሚገባ የተወጣ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን አባት ነው።

- ቅዱስ አትናቴዎስ በአርዮሳውያን ሴራ አራት ጊዜ የተሰደደ እና ብዙ መከራ የተቀበለ ሲሆን ለትውልድ እየተላለፉ ቤተ ክርስቲያንን የሚያለመልሙ ድንቅ የነገረ ሃይማኖት መጻሕፍትን ጽፏል።
- ከነዚህ መካከል “በእንተ ሥጋዌ”፣ “የአርዮሳውያን መቃወሚያ (Against Arians)”፣ “በእንተ ስደት” ተጠቃሾች ናቸው። በተጨማሪም የቅዱስ እንጦንስን ገድል የጻፈው ቅዱስ አትናቴዎስ እንደሆነ ይታወቃል።
- ይህ አባት ሌሎች በርካታ መጻሕፍትን እየጻፉ እና ከነገሥታት እና ባለሥልጣናት ሳይቀር የሚመጣበትን መከራ እየተቀበለ ለቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መጠበቅ እስከ መጨረሻዋ ሰዓት ድረስ ታግሏል።
- በዚህ ጽናቱም “ዓለሙ አትናቴዎስን ጠልቶታል፤ አትናቴዎስም ዓለሙን ጠልቶታል” ለመባል በቅቷል።
- ዘመን ገጠሙ የነበረው ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ “የቤተ ክርስቲያን ዓምድ” ይለዋል።
- የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ “የኦርቶዶክሳዊነት አባት (Father of Orthodoxy)” ትለዋለች።
- ይህ ታላቅ የሃይማኖት አርበኛ በሰባ አምስተኛ ዓመቱ በአርባ ስድስተኛ ዓመተ ፕትርክናው ግንቦት 7 ቀን 373 ዓ.ም ድካምና ውጣ ውረድ የተመላውን የዚህን ዓለም ሕይወት በአስደናቂ ሁኔታ ፈጸመ።

የቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ትምህርቶች አጭር ዳሰሳ

- ማንም የነገረ መለኮት ተማሪ ሊያጠናቸው ከሚገባ መጻሕፍት መካከል የቅዱስ አትናቴዎስ መጻሕፍት ግንባር ቀደም ናቸው።
- እነዚህ መጻሕፍት ነገረ ድኅነትን ማዕከል ያደረጉ እና ምሥጢረ ሥላሴን እና ሥጋዌን በጥልቀት የሚያብራሩ ናቸው።
- ከሰፊው ትምህርቱ ለማሳያ ያህል ጥቂቶቹን ከዚህ በታች እናቀርባለን።

የቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ትምህርት ስለ ጌታችን የባሕርይ አምላክነት

- አርዮስ “ወልድ ፍጡር በመለኮቱ” በማለቱ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችንም ለምንፍቅናው እንዲመቸው እያደረገ በመተርጎም ቤተ ክርስቲያንን ሲያውክ ቅዱስ አትናቴዎስ ከእግዚአብሔር ባህርያት እና ከነገረ ድኅነት በመነሳት እና መጻሕፍቱንም ሐዋርያዊ በሆነው ትውፊት በመተርጎም ድንቅ በሆነ ጥበብ መልስ ሰጥቶታል።
- አርዮስ “አናጺ ህንጻ ከመሥራቱ በፊት መዶሻ እንደሚሠራ እግዚአብሔርም ወልድን (ጥበብን) መጀመሪያ ፈጥሮ ፈጠረበት” ላለው መልስ ሲሰጥ እንዲህ ብሏል።

- “እግዚአብሔር ፍጥረታትን ይፈጥርበት ዘንድ ሌላ ፍጡር ፈጠረ የሚለውን የልብወለድ ክህደት ማን አቀበላችሁ? ከየትስ አገኛችሁት? ሌሎቹን ፍጥረታት የሚፈጥርለት መፍጠር ለምን ያሻዋል? በመፍጠር እንዳይደክም ነው ብትሉ ይህ ከባድ ስህተት ነው። ኢሳይያስ “አላወቅህምን? አልሰማህምን? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፥ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው፤ አይደክምም፥ አይታክትም፥ ማስተዋሉም አይመረመርም። ለደካማ ኃይልን ይሰጣል፥ ጕልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል።” ያለውን የመጽሐፍ ቃል ለሚያውቅ ይህ ክህደት ነው።(ኢሳ. 40÷28) ፍጥረታትን በቀጥታ መፍጠርን ዝቅ እንደማለት ስለቆጠረው ነው ማለትም ሌላ ጠማማ ትምህርት ነው። ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብጽ የወረደ፣ ለአብርሃም ብሎ ሳራን ለጠበቅ አቤሜሌክን ከስህተት የመለሰ፣ እርሱ ሰው ሲሆን ከሙሴ ጋር ፊት ለፊት የተነጋገረ ወደ ሲና ተራራም የወረደ፣ በረቂቅ ጸጋው ለህዝቡ ከአማሌቃውያን ጋር የተዋጋ እርሱ ከኩራት የተነሳ ዓለምን የሚፈጥርለት ጠቢብና እና ኃያል ፍጥረት ቀድሞ ፈጠረ እንዴት ይባላል? በእግዚአብሔር ዘንድ ኩራት የለም።”
- /Defense of the Nicene Creed, 7/

የቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ትምህርት ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ እና ነገረ ድኅነት

- ቅዱስ አትናቴዎስ ከሐዋርያት እና ከቀደሙ አበው የተቀበለውን የነገረ ድኅነት ትምህርት ማዕከል አድርጎ ነበር መጻሕፍትን የሚተረጉመው። አርዮስን የረታውም የአርዮስ አስተምህሮ ነገረ ድኅነትን ከንቱ የሚያደርግ አደገኛ ትምህርት መሆን በማሳየት ነበር። “በእንተ ሥጋዌ” በተባለው መጽሐፉ ስለ ሥጋዌ ምሥጢር እና ስለ ድኅነት እንዲህ ይላል።
- “የቸርነቱን ብዛት ያሳየን ዘንድ እና ይጎበኘን ዘንድ ምንም እንኳ በሁሉ ያለ እና ሁሉን የሞላ ቢሆንም የሰውን ባሕርይ በመንሳት የማይታየው የማይለወጠው እና ረቂቁ የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኛ መጣ። የሰው ዘር ወደ ጥፋት እያመራ እንደሆነ አይቶ፣ ሞት በሰው ላይ ኃይሉን አጽንቶበት የእጁ ሥራ ወደ ጥፋት እየሄደ እንደሆነ ተመልክቶ፣ የሰው ዘር ከኃጢአት ላይ ኃጢአት እየጨመረ ወደ ጥፋት መፋጠኑን አይቶ፣ ሞት በሁሉም ላይ ጥላውን አጥልቶ ቢያየው ለሰው ዘር ራራ፤ በድካማችን ሳይተወን ምህረቱን ሰጠን። ወደ ጉስቁልናችን ወረደ፤ ሞት ገሸሽ ሆኖ እንዲቀጥል እና የአባቱ የእጅ ሥራዎች የሆንን እኛን እንዲያጠፋን አልፈቀደም፤ ስለዚህም ከእኛ ጋር አንድ የሆነ የኛን ሥጋ ለበሰ። ይህን ርኩሰት ከሌለባት እና ወንድ ከማታውቅ ድንግል በራሱ ጥበብ ቤተ መቅደስ አድርጎ የሠራውን የራሱን ሥጋ እንደመሳሪያ ተጠቅሞ በሞት እጅ በተያዙት ፈንታ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ለአባቱ አቀረበ። የሰው ዘር ወደ መጥፋት (Corruption) እያመራ ነበር እና በለበሰው ሥጋ በመሞት እና ሞትን ድል አድርጎ በመነሳት ሰው የሚሄድበት አዲስ የሕይወት መንገድን መሠረተ።”

የቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ ሕይወቱ እና ትምህርቱ አጭር ዳሰሳ

7.1.1 የቅዱስ ባስልዮስ ዜና ሕይወት

- ቅዱስ ባስልዮስ በቀጰዶቂያዋ ቂሳርያ በ330 ዓ.ም አካባቢ ተወለደ። አባቱ ባስልዮስ ይባላል፤ እናቱ ደግሞ ኢሚሊያ ትባላለች።
- ማክሪና የምትባል በሃይማኖቷ የበረታች እህት ነበረችው።
- ከታላቁ አባት ከቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ጋር አራት ወንድሞች እና አራት እህቶች ነበሩት።
- አባቱ ባስልዮስ በንግግር ክህሎቱ የታወቀ መምህር እና ሐብታም ክርስቲያን መሆኑ ለባስልዮስ ጥሩ የክርስቲያናዊ አስተዳደግና እውቀት እንዲኖረው አስተዋጽኦ አድርጓል።
- ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ የቀጰዶቂያ አባቶች ተብለው ከሚጠሩት አባቶች (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙና ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ) አንዱ ሲሆን በመጀመሪያ ወደ ቁስጥንጥንያ ተጉዞ የህግና የንግግር ክህሎት ተምሮ በነዚህ የዘመኑ ጥበባት እንደ አብዛኛዎቹ ዘመን ገጠም አበው እስከ አስተማሪነት ብቃት የደረሰ ነበር።
- በኋላ በሴት አያቱና በእህቱ በጎ ተጽህኖ ምክንያት በ357 ዓ.ም አካባቢ የፍልስጥኤምን፣ የሶርያን፣ የግብጽን እና የሞሶፖታሚያን ገዳማውያን ተዟዙሮ ከተመለከተ በኋላ የምነና/ምንኩስና ህይወትን ጀመረ።
- ቅዱስ ባስልዮስ ትጎርምት የሚወድ መነኮሴ እንደነበረ ይነገራል።

- በመጀመሪያዎቹ የምንኩስና አመታት በስነ መለኮት ውዝግቦች ብዙም ይሳተፍ አልነበረም። በኋላ ግን “ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ከአብ ያንሳሉ” የሚሉ አርዮሳውያን እና ተረፈ አርዮሳውያን ቤተ ክርስቲያንን ሲያውኳት የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ለማስጠበቅ በግንባር ቀደምነት ተሰልፎ ተጋድሎ ፈጽሟል።
- በቅስና እና በኋላ በ370 ዓ.ም ሊቀ ጳጳሱ ባስልዮስ ሊያርፍ በእርሱ ተተክቶ የቂሳርያ ሊቀ ጳጳስ በመሆን ቤተ ክርስቲያንን አገልግሏል።
- ቅዱስ ባስልዮስ ተዘዋውሮ ያያቸውን የምንኩስና ሥርዓቶች በአካባቢው ማስፋፋቱ ይነገራል።
- በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ተቀባይነት ያገኘ ጸሎተ ቅዳሴ ደርሷል።
- እስካሁኑ ዘመን የደረሱ በሃይማኖተ አበው የተሰበሰቡ ትምህርቶቹ እና “በእንተ መንፈስ ቅዱስ” የተሰኘው መጽሐፉ ተጠቃሾች ናቸው።፤
- ከጓደኛው ከቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ እና ከወንድሙ ከቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ጋር ሆነው የዘመኑን የመናፍቃን ወዝብ የመከቱ እና ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት ብርሃን የሆኑ አበው ናቸው።
- በዚህ የጎበረት ተጋድሎአቸውም የነገረ አበው ሊቃውንት “ቅድስት ሥላሴን በትምህርታቸው ያከበሩ ሦስቱ አባቶች (trinity who glorified the Holy Trinity)” እያሉ ይጠሯቸዋል።

- የቅዱስ ባስልዮስ መጻሕፍት ይዘት

- ገዳማዊ ህይወትን የተመለከቱ ጽሑፎች፡- የገዳማዊ ህይወትን ምንነት፣ ተጋድሎ እና የማኅበር መመሪያዎችን አስመልክቶ የጻፋቸው ድርሳናት ናቸው።

- ዶግማ ነክ ጽሑፎች
  - ዘለፋ ዘኢዩኖሚዎስ (Against Eunimius)፡- የመንፈቀ አርዮሳዊውን የኢዩኖሚዎስን ትምህርት በመቃወም የጻፈው እና አምስት ክፍሎች ያሉት መጽሐፍ ነው።
  - በእንተ መንፈስ ቅዱስ (On the Holy Spirit):- መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር የባህርይ አምላክ መሆኑን እና አምልኮ የሚገባው መሆኑን ያስተማረበት እና መቅዶንዮስና ሌሎች ተረፈ አርዮሳውያን “መንፈስ ቅዱስ እፀፅ ፣ ፍጡር” ለሚለው ትምህርታቸው እንዲመቻቸው እያጣመሙ የሚተረጉሟቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ንባባት የተረጎመበት መጽሐፍ ነው።

- መጽሐፈ አክሲማሮስ፡- የስድስቱን ቀናት ሥነ ፍጥረት ያብራራበት።
- የትርጓሜ መጻሕፍት ሥራዎች
- ስብከቶች፡- ቅዱስ ባስልዮስ በዶግማ፣ ሥነ-ምግባር እና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የሰበካቸው ስብከቶች ናቸው።
- የተለያዩ ደብዳቤዎች፡- ወደ ተለያዩ ቦታዎች እና አባቶች የተላኩ ደብዳቤዎች እና መልእክቶች ያካትታል።
- ቅዳሴ ባስልዮስ፡- የሐዋርያትን የቅዳሴ መዋቅር እና ሥርዓት ተከትሎ የደረሰው ጸሎተ ቅዳሴ ነው። ይህ የቅዱስ ባስልዮስ ቅዳሴ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት የታወቀ ነው።
- ሌሎች የጠፉ መጻሕፍት

•የቅዱስ ባስልዮስ ትምህርቶች አጭር ዳሰሳ

- ከላይ እንደዘረዘርነው ቅዱስ ባስልዮስ በትምህርቱ ብስለት “ታላቁ ባስልዮስ” እስከመባል የደረሰ እና በማስተማር ብዙ የደከመ ሰው ነው።
- ስለዚህ ትምህርቶቹን በሚገባ ለመረዳት መጻሕፍቱን በማስተዋል ማንበብ ተገቢ ነው።

ከዚህ በታች ለማሳያ ያህል ከትምህርቶቹ ጥቂት እናቀርባለን።

- ቃላትን በማራቀቅ ብቻ ስለ እግዚአብሔር ህላዌ በደንብ እናውቃለን የሚሉ እነ ኢዩኖሚዎስን የመሳሰሉ መናፍቃንን በጽሑፎቹ እንዲህ እያለ ይገስጻቸዋል።
- “ይህ ምን ዓይነት ትዕቢት ነው! ይህ ምን ዓይነት ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ ነው! የእግዚአብሔርን ባሕርዩን አውቀነዋል የሚሉ መናፍቃንን ተመልከቷቸው! ራሳቸውን ከፍ ከፍ ሲያደርጉ “ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ” ያለውን (ዲያብሎስን) መሰሉት። (ኢሳ. 14÷13) እነርሱ ከዚህም አልፈዋል፤ አወቅን የሚሉት ከዋክብትን አይደለም፤ ሰማያትንም አይደለም፤ በባሕርዩ አውቀነዋል የሚሉት የዓለማትን ፈጣሪ ነው! እስኪ እንጠይቃቸው፤ የእግዚአብሔርን ባሕርይ እንዴት ነው ያወቁት? በሰው ተፈጥሮ ውስጥ ያለውን አእምሮ ተጠቅመው ነው? ይህ ከሆነ እግዚአብሔር መኖሩን እንጂ ባሕርዩ ምን እንደሆነ ለማወቅ እንደማያስችል የታወቀ ነው። ታዲያ መንፈስ ቅዱስ ከገለጣቸው ትምህርቶች ነው? የትኛው ትምህርት ነው የእግዚአብሔርን ባሕርይ መመርመር ይቻላል የሚል? የት አገኙት? እግዚአብሔር የተደበቀ ምስጢሩን የገለጠለት ታላቁ ዳዊት “እውቀትህ ከእኔ ይልቅ ተደነቀች፤ በረታች÷ ወደ እርስዋም ለመድረስ አልችልም።” አላለምን? (መዝ. 139÷6)...የፍጥረታትን ባሕርይ እንኳ መመርመር እንዴት ይቻላል?”

- በመዝሙረ ዳዊት መዝሙር 13÷1 ላይ የሚገኘውን “አቤቱ÷ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል? በተቀደሰውም ተራራህ ማን ይኖራል?” የሚለውን በተረጎመበት መጽሐፉ ስለ መንፈሳዊ ሕይወት እንዲህ ይላል፡-
- “አቤቱ÷ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል? በተቀደሰውም ተራራህ ማን ይኖራል?” በድንኳን ማደር እንግድነትን የሚያመለክት ነው። ወደ ሌላ የተሻለ ነገር መገስገስን አሁን ባሉበት ሁኔታ ግን ተደላድሎ አለመቀመጥን ያመለክታል። የቅዱሳን አካሄድ ለዚህ ዓለም የእንግድነት ለሚመጣው ዓለም ደግሞ መሸጋገሪያ ነው። ዳዊት “እኔ በምድር ላይ መጻተኛ ነኝና÷ እንደ አባቶችም እንግዳ ነኝና።” ያለው ይህንን ነው። አብርሃም በምድር መጻተኛ ነበር፤ እግሩን የሚያስቀምጥበት ቦታ ስላልነበረው የመቃብር ቦታ እንኳ ያገኘው ገዝቶ ነው። ...ምድራዊ ነገሮች የርሱ ገንዘቦች እንዳልሆኑ ተረድቶ እንዲያበላሹት የማይፈቅድላቸው ምስጉን ነው።...ምድራዊው ነገር የእርሱ እንዳልሆነ ቆጥሮ ቦታ የማይሰጥ፣ ሃብት ንብረት ጊዜያዊ መሆኑን የሚረዳ ፣ጤና ዘላቂ አለመሆኑን የሚያስታውል፣ የሰው ክብር አብቦ የማይዘልቅ ጊዜያዊ መሆኑን የሚረዳ ሰው ማግኘት ግን ጭንቅ ነው።
- “...ከዚያ ቀጥሎ “በተቀደሰው መቅደሱስ ማን ያድራል?” ይላል። በሥጋው እንግዳ እና መጻተኛ የሆነ ሰው በዚያ ተራራ፣ በሚያበራው እና ጸዳሉ በሚያንጸባርቀው በሰማያዊው አገር፣ ቅዱስ ጳውሎስ “ነገር ግን ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኃል÷ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም÷ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት÷ በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር” ብሎ በተናገረለት አገር ያድራል። (ዕብ. 12÷22)”

- <u>የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሕይወቱ እና ትምህርቱ አጭር ዳሰሳ</u>
  - <u>የአባ ጊዩርጊስ ዘጋስጫ ዜና ሕይወት</u>
- አባ ጊየርጊስ ዘጋስጫ ከአባቱ ከሕዝበ ጽዮን ከእናቱ ከእምነ ጽዮን በዛሬው በወሎ ክፍለ ሀገር ቦረና በጥንቱ ወለቃ ወረዳ ሸግላ በተባለ ቦታ በ1357 ዓ.ም ተወለደ።
- የካህናት ወገን የሆኑት እናትና አባቱ በሕግ እግዚአብሔር የጸኑ ደጋግ ሰዎች እንደነበሩ በገድሉ ተጽፏል።
    - የአባ ጊዮርጊስ የትምህርት ሂደት
- ታሪካቸው ከቅዱስ ያሬድ ጋር ይመሳሰላል።
- አባቱ ሕዝበ ጽዮን ለትምህርት ሲደርስ ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ወስዶ ይማር ዘንድ አባ ሠረቀ ብርሃን ለተባሉ መምህር ቢሰጠውም ትምህርት በቀላሉ ሊገባው እንዳልቻለ ገድሉ ይተርካል።
- በዚህም ምክንያት ገዳሙን በጉልበት ስራ እያገለገለ እና ከእመቤታችን ስዕል ስር እልፍ እልፍ እየሰገደ ትምህርቱን ትገልጥለት ዘንድ እየተማጸነ ቆየ።
- በመጨረሻም እመቤታችን ዑራኤል መልአክን አስከትላ መጥታ እንደ ነብዩ እዝራ ጽዋዐ ልቡና /የዕውቀት መጠጥ/ እንዳጠጣችው ገድሉ ይመሰክራል።
- ከዚህ በኋላ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የመጻሕፍት ምስጢር ተገልጦለት መጻሕፍትን እንደደረሰ እና ኦሮውም በታላቅ ቅድስና ያጌጠ እንደበር ገድሉ ይናገራል።

- በዚህ እውቀቱ ምክንያት ይመቀኙት ከነበሩ ሰዎች እና ከመናፍቃን ብዙ መከራን ተቀብሏል።
- በዘመኑ የነበሩ ነገሥታት ብዚ ጊዜ አሳድደውታል፤ አስደብድበውታል።
- በዚህም ምክንያት በተለያዩ በሽታዎች እንደተሰቃየ እና ሳይሸመግል ገና በ60 ዓመቱ አንዳረፈ በገድሉ ተጽፏል።
- አባ ጊዮርጊስ በመጽሐፍት አዋቂነቱ እና በቅድሰናው የተመሰከረለት ሰው ስለነበር በዘመኑ በሀገራችን የነበሩ አይሁዶች እና ሌሎች መናፍቃን የሃይማኖት ጥያቄ ሲያነሱ በግንባር ቀደምትነት ይሰለፍ ነበር።
- ከነዚህ መናፍቃን መካከል የሆነ አንዱ አይሁዳዊ “ጌታችሁ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነ አልዓዛርን የት ቀብራችሁት ብሎ ለምን ጠየቀ?›› ብሎ በጠየቀው ጊዜ አባ ጊዮርጊስ “እግዚአብሔር አብ በኦሪት ለምን “አዳም ሆይ ወዴት አለህ? ብሎ ጠየቀው አብርሃምንስ ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት ብሎ ለምን ጠየቀው?” በማለት እንዳሳፈረው ይነገራል።
- አባ ጊዮርጊስ ከዕውቀቱ ባለፈ ሕይወቱ የቅድስና እንደነበረ ገድሉ ይናገራል።
- በዚህም የተነሣ በሕይወት እያለ ቅዱስ ጴጥሮስና ጳውሎስ ተገለጠው እንዳነጋገሩት ደብዳቤም በአውሎ ነፋስ እንዳላከ በገድሉ ተጽፏል።

የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሥራዎች

- በርካታ የድርሰት ሥራዎችን በማበርከት ቅዱስ ያሬድን እና አባ ጊዮርጊስን የሚተካከል ሰው በኢትየጵያ ቤተ ክርስቲያን አልተነሳም።
- የመጽሐፉቹ ብዛት በትክክል ባይታወቅም በገድሉ ውስጥ የተጠቀሱት የሚከተሉት ናቸው።
- አርጋኖን፡- ይህ መጽሐፍ የእመቤታችን ምስጋና ነው። መጽሐፉ በሰባት ቀናት የተከፈለ ነው።
- እንዚራ ስብሐት፡- ይህም መጽሐፍ የእመቤታችን ምስጋና ነው። በግእዝ ፊደላት ቁጥር እመቤታችን ያመሰገነበት እና ምስጢረ ሥጋዌን ያመሰጠረበት ነው።
- ውዳሴ ሐዋርያት፡- ይህን መጽሐፍ አባ ጊዮርጊስ በእስር ቤት ሆኖ እንደጻፈው ይነገራል።
- መጽሐፈ ምሥጢር፡- ይህ መጽሐፍ የአባ ጊዮርጊስ የነገረ ሃይማኖት እውቀት በስፋትና በጥልቀት የተንጸባረቀበት መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ የመናፍቃንን ትምህርት ለመቃውም የተጻፈ መጽሐፍ ነው። ይህን መጽሐፍ አምስት ፈጣን ጸሐፊዎች እርሱ በቃል እየነገራቸው እረፍት ሳያደርጉ በሦስት ቀን እንደጻፉት ይነገራል። እነዚህ ጸሐፊዎች የየድርሻቸውን ጠንቅቀው ጽፈው በአንድ አደረጉት። አባ ጊዮርጊስም ጽሑፉን ተመልክቶ አደነቀ፤ “እኔ የዚህን መጽሐፍ ቃል አልተናገርኩም፤ መንፈስ ቅዱስ በእኔ አፍ ተናገረ እንጅ” ሲል መመስከሩን ገድሉ ይገልጣል።

- መጽሐፈ ሰዓታት ዘመዓልት ወዘሌሊት፡- መጽሐፈ ሰዓታት ከስያሜው መረዳት እንደሚቻለው የሌሊት ምስጋናና የቀን ምስጋና ተብሎ በሁለት ይከፈላል። መጽሐፈ ሰዓታት የተባለበት ምክንያት በየሰዓቱ የሚጸለይ ምስጋናን የየዘ በመሆኑ ነው።
- መጽሐፈ ብርሃን፡- ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን መንገድ እና ክብረ ድንግልን ለመግለጽ ያዘጋጀው መጽሐፍ ነው። ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብም ‹መጽሐፈ ብርሃን› በሚል ስያሜ መጽሐፍ የጻፈ ቢሆንም ከዚህ መጽሐፍ ጋር ግን በስያሜ እንጂ በይዘት ይለያያሉ።
- ፍካሬ ሃይማኖት፡- አባ ጊዮርጊስ ይህን መጽሐፍ ያዘጋጀበት ምክንያት የዐፄ ዳዊት ጦር አዛዥ የነበረው ቴዎድሮስ ስለቀናች ሃይማኖቱ በጠየቀው ጊዜ መልስ ይሆን ዘንድ እንደሆነ ገድሉ ይናገራል።
- ቅዳሴያት፡- አባ ጊዮርጊስ በወርኀ ጽጌ የሚቀደስ ቅዳሴ መድረሱ እና ይህም በአንዳንድ ገዳማት ይቀደስ እንደነበር ይነገራል። ሌሎችም ያልታተሙ ቅዳሴዎች እንዳሉት ጥናት ያደረጉ ሰዎች ይናገራሉ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አብዛኛዎቹ ቅዳሴያት በይዘት መመሳሰላቸው ምናልባትም ደራሲያቸው አባ ጊዮርጊስ ሊሆን ይችላል የሚል ጥርጣሬ ያሳደረባቸው ሰዎች አሉ። ነገር ግን ለቀጣይ ጥናት የሚጋብዝ እንጂ በርግጠኝነት መናገር የሚቻል አይደለም።
- ውዳሴ ስብሐት ፣ ውዳሴ መስቀል፣ ኑኅተ ብርሃን፣ ሕይወተ ማርያም ፣ተአምረ ቅዱሳን፤ ጸሎት ዘቤት ቤት
- እስካሁን ድረስ ያሉት ምንጮች የአባ ጊዮርጊስ ድርሰቶች ቁጥራቸው ከአርባ በላይ እንደሆኑ ይገለጣሉ። ከላይ የተጠቀሱት በስም የሚታወቁት ብቻ ናቸው።

- የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ትምህርቶች ዳሰሳ

- የአባ ጊዮርጊስ ጥልቅ የነገረ መለኮት ዕውቀት ከድርሰቶቹ በግልጥ ሊታይ የሚችል ነው። በአባ ጊዮርጊስ ትምህርቶች ውስጥ የሚታየው ነገረ መለኮትን በእምነት በተሞላ ልቡና እና ግልጽ በሆነ ቋንቋ መግለጥ ይህ አባት ትምህርቱን ከጥንተውያን አበው ትውፊት የተቀበለውና በቅድስና ሕይወቱ ያረጋገጠው መሆኑን ይመሰክራል።
- በመጽሐፉ ምስጢር ድርሰቱ መናፍቃንን ሲገስጽ ‹ራሳቸው የእግዚአብሔርን ቃል የተጠሙ ሲሆኑ እንዴት መምህራን ለመባል ቻሉ?›› ይላል። በእውነትም የቤተ ክርስቲያን መምህር ለመባል መጀመሪያ በእግዚአብሔር ቃል መረስረስ እንደሚገባ ራሱ አባ ጊዮርጊስ ምስክር ነው። አንድን ትምህርት ለማስረዳት ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ራዕየ ዮሐንስ ድረስ የሚመላለሰው አባ ጊዮርጊስ ምን ያህል የቅዱሳን መጻሕፍት ዕውቀት እንዳለው ድርሰቶቹ ምስክሮች ናቸው።
- ከመጻሕፍት ዕውቀቱም በተጨማሪ ውብ የቋንቋ ችሎታውና ለተመስጦ ቅርብ የሆነ ልቡናው በእውነትም ከቅዱሳን ሊቃውንት ተራ መሰለፍ እንደሚገባው ማሳያዎች ናቸው።

የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የምስጢረ ሥላሴ አስተምህሮ

- አባ ጊዮርጊስ በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርቱ እንደ ቅዱስ አትናቴዎስ ካሉ ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጋር በእጅጉ የተስማማ ነው።
- በድርሰቶቹ የምናገኘው የምስጢረ ሥላሴ ትምህርቶቹ የአንባቢን ነፍስ እንደ እሳት ወላፈን በሚያሚሙቅ የአገላለጥ ችሎታ እና የቋንቋ ውበት ያጌጡ መሆናቸው ይህን ጥልቅ የነገረ እግዚአብሔር ምሥጢር ለማሰተማር እግዚአብሔር አንደበቱን በውብ የቋንቋ ውበት ልቡናውን በቅድስና ምሥጢር ያስታጠቀው አባት መሆኑን የሚመሰክሩ ናቸው።
- ምንም እንኳን ከዚህ በኋላ በምንጠቅሳቸው የድርሰቱ ክፍሎች ግእዙንና አማርኛውን ማቅረብ ከጽሑፉ አላማ እና ምጣኔ አንጻር አስፈላጊ ባይሆንም አባ ጊዮርጊስ በጻፈበት በግእዝ ቋንቋ ድርሰቱ ያለውን የአገላለጥ ውብት ለማሳየት አልፎ አልፎ በግእዝና በአማርኛ ለመጥቀስ እንሞክራለን።

አባ ጊዮርጊስ በመጽሐፉ ምስጢር የፋሲካ ዓርብ ምንባቡ መጀመሪያ ላይ እንዲህ ይላል፦

- ብስመ እግዚአብሐር ዘይሜለስ በተዋሕዶቱ ወይትወደስ በትሥልስቱ አኃዜ ዓለም በመንግሥቱ ምሉአ ኩለሄ በመለኮቱ አበኩሉ በኂሩቱ ረኁቀ መዐት በትእግሥቱ መጽደቄ ኃጥአን በሥምረቱ መቅለሌ ዕጹብ በክሂሎቱ ጠቢበ ጠቢባን በተኬንዎቱ ወአልቦ ዘይትቃወማ ለጽንዐ መዓቱ ዘእንበለ ኃይለ አድኅኖቱ ወአልቦ ዘያቆርራ ለእሳተ ቅንዐቱ ዘአንበለ ጠለ ሣህሉ ወምህረቱ ዘይወርድ እመዝገበ ቤቱ ለዓለም ዓለም አሜን ወአሜን›

ትርጉሙም፡-

- ብአንድነቱ በሚቀደስ ፣በሦስትነቱም በሚወደስ፣ ዓለምን በመንግሥቱ በያዘ፣ በመለኮቱም በቦታ ሁሉ በመላ፣ በቸርነቱ የሁሉ አባት በትዕግሥቱም ከቁጣ የራቀ፡ በፈቃዱም ኃጥአንን የሚያጸድቅ፣ በቻይነቱም ጭንቅን የሚያቀልል፣ በጥበቡም የጥበበኞች ጥበበኛ በሆነ፣ ከማዳኑ ኃይል በቀር የቁጣውን ጽናት የሚቋቋማት በሌለ፣ ከቤቱ መዝገብ ከሚወጣ ከይቅርታውና ከርኅራኄው በቀር የቅናቱን እሳት የሚያቀዘቅዛት በሌለ በእግዚአብሔር ስም ለዘላለሙ አሜን አሜን› ማለት ነው።
- አባ ጊዮርጊስ በምሥጢረ ሥላሴ አስተምህሮው የሥላሴ አካላትን የሚያበላልጡ /አብ ከወልድ ይበልጣል፣ ወልድ ደግሞ ከመንፈስ ቅዱስ ይበልጣል/ የሚሉ መናፍቃንን አጠብቆ ያወግዛል።

በመጽሐፉ ምሥጢር የጌና ስብከት ምንባቡ ላይ እንዲህ ይላል፡-

- “አብ ብርሃን እንደሆነ ወልድም ለሰው ሁሉ የሚያበራ ብርሃን ነው። ወልድ ብርሃን እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም ፍጹም በሆነ አንድ ጸዳል ያለ ብርሃን ነው። አብ የማይዳሰስ እሳት እንደሆነ ወልድም የማይያዝ እሳት ነው። ወልድ የማይያዝ እሳት እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም በሃይማኖት ሙቀት ቤተ ክርስቲያንን የሚያሞቃት እሳት ነው። አብ የማይታይ ኃይል እንደሆነ ወልድም ሰው በመሆኑ ካልሆነ በቀር የማይገለጥ ኃይል ነው። አብ ፍጹም አምላክ እንደሆነ ወልድም ፍጹም አምላክ ነው። ወልድ ፍጹም አምላክ እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም በአንድ ጎብር መልክእ ያለ ፍጹም አምላክ ነው።”

- በሌላኛው ድርሰቱም አንዲህ በማለት የሥላሴን ምሥጢር በጸሎትና በምስጋና መልኩ ያቀርባል፡-
- “ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘበተዋሕዶ ይሤለስ እምኀበ ትጉሃን ይትቄደስ። እሳተ ሕይወት ዘኢይትገሠሥ ወዘኢይትጤየቅ ለዓይን ረቂቅ መንፈስ። ንሰግድ ለትስልስቱ አሐተ ስግደተ ወሎቱ ናቄርብ ስብሐታተ”
- ትርጉም፡-
- “ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር በአንድነቱ ሦስተነት ያለው በትጉሃን ዘንድ የሚመሰገን የማይዳሰስ የሕይወት እሳት በዓይን የማይመረመር ረቂቅ መንፈስ። ለሦስትነቱ አንዲት ስግደትን እንሰግዳለን፤ ለእርሱም ምስጋና እናቀርባለን።”ማለት ነው። / መጽሐፈ ሰዓታት/

የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የምሥጢረ ሥጋዌ አስተምህሮ

- አባ ጊዮርጊስ በጥብቅና እና ሌሎች መጽሐፍቶቹ አብዝቶ ካስተማረባቸው ርእሶች አንዱ መሥጢረ ሥጋዌ ነው። የተግሳጽ መልስ ከጻፈባቸው መናፍቃን መካከል ንስጥሮስ፣ ሮጥየስ፣ ሳዊሮስ ዘሕንድክየ እና ታአደስዮስ ዘእለእስክንድርያ፣ አቡርዮስ፣ እፍረክስ፣ ፍልብያኖስ እና ሌሎችም በዋነኝነት ምንፍቅናቸው በምሥጢረ ሥጋዌ ላይ በመሆኑ ስለርሱ አብዝቶ ተናግሯል።
- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሁለት አካል ሁለት ባህርይ አለው ብሎ ለተነሳው ለንስጥሮስ በሰጠው መልስ የምሥጢረ ሥጋዌን ነገር እንዲህ ይናገራል፡-
- “ቀድሞ ብቻውን እግዚአብሔር ከብቻ ከእግዚአብሔር እንደተወለደ በኋለኛው ዘመን ብቻውን የሚሆን የእግዚብሔር ልጅ ብቻዋን ከምትሆን ከዳዊት ልጅ ተወለደ። በመጀመሪያ የማይታይ እርሱ ከማይታየው ተወለደ፤ በኋላም የማይያዝ የሕይወት እሳት ከምትዳሰስ ሥጋ ተወለደ። በመጀመሪያ የሀልዎቱ መጀመሪያ ሳይታወቅ ተወለደ፤ በኋላም የዘመናት ፈጣሪ አመታትንም የሚወስን እርሱ ዕድሜዋ አሥራ አምስት ዓመት ከሆነ ከታናሽ ብላቴና ተወለደ። የመጀመሪያ ልደቱን ምስጢር የኋለኛ ልደቱንም ድንቅ አደረገ።”/ መጽሐፈ ምስጤር የጌና ምንባብ/

- ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባህርይ አለው ለሚል ለሮሙ ሊቀ ጳጳስ ለልዮን በሰጠው መልስም፡-
- “ባለመድኃኒት በድውዮች ሴት ልጅ ዘንድ አደረ፤ ከእርሷም ምድራዊት ሥጋን ተዋሐደ። ለድውዮችም ፈውስ በሚሆን ግንዘብ ከመለኮቱ ጋር አንድ አደረገው ባለመድኃኒት ከሰማያት ሰማይ መጥቷልና የፈውስ እንጨትም በዳዊት ቤት ተገኘ፤ ያለመለኮት ከሥጋ ጋር መዋሐድ ፈውስ እንደማይገኝ ባለመድኃኒቱ ዐወቀ፤ ስለዚህም ራሱን ሰው ለመሆን ሰጠ። ታማሚስ ለራሱ ፈውስን ያደርግ ዘንድ አይቻለውም፤ ነገር ግን በሚድንበት ግንዘብ መድኃኒት እንዲያደርግለት ባለመድኃኒቱን ይማልደዋል።”
- በመጨረሻም “የክርስቶስ ሥጋው ከሰማይ ወረደች” ለሚሉ ለአፍቲኪሳውያን በሰጠው የተግሳጽ ምላሽ ስለ እግዚአብሔር ልጅ ሰው መሆን የተናገረውን በመጥቀስ የአባ ጊዮርጊስ የሥጋዌ ትምህርት በአጭሩ ያቀረብንበትን ርዕስ እንፈጽማለን ፡-

- “እናንተ ሰነፎችና ልባችሁ ከማመን የዘገየ አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ ብሎ መናገርን እንዳስቀደመ ከአዳም ዘር ሰው ሆኖ እንደተወለደ ዕወቁ። መድኃኒታችን ከለበሰው ከአዳም ሥጋ በቀር የአዳም እንደ እግዚአብሔር መሆኑ ምንድን ነው? በዚያችም ሥጋ በምድር ላይ ጉስቁልናን ለበሰ፤ ያችንም ሥጋ በሰማያት ጌትንትን አለበሳት።
- “ስለ ትሕትና ነገር መናገርን እናስቀድም፤ ኃይል በሴት ማኅፀን አደረ፤ እሳትም በሥጋና በደም መጐናጸፊያ ተጠቀለለ። ሕፃናትንም የሚስል በሕፃናት መልክ ተሣለ፤ የሔዋን አባት ከሔዋን ሴት ልጅ ተወለደ፤ በኪሩቤል ላይ የሚቀመጥ በጉልበት ታቀፈ፤ እሳት በተሣለባቸው በአራቱ እንሰሳ ላይ የሚጫን በላምና በአህያ መካከል ተኛ። ሥጋዊን ሁሉ የሚመግበው የጡት ወተትን ተመገበ። በጊዜና በዘመናት የሸመገለ በየጥቂቱ አደገ፤ በታናሽነታቸው ጊዜ ሕፃናትን የሚጠብቃቸው በሜዳ ላይ ዳኸ፤ ለዓመታቱ ቁጥር ጥንት የሌለው በሰው መጠን ጐለመሰ፤ ተራሮችን በኃይል የሚያቆማቸው ደከመ፣ ወዛም። ኪሩቤል ሊነኩት ሱራፊልም ሊዳስሱት የማይቻላቸው እግሮቹን በአመንዝራይቱ ልብሶቹንም ደም በሚፈስሳት ሴት ተዳሰሰ”
- /መጽሐፈ ምሥጢር የዓርብ ስቅለት የዘጠኝ ሰዓት ምንባብ/

የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የነገረ ድኅነት አስተምህሮ

- ከጥንታውያን አበው ጀምሮ እንደምናየው የክርስትና ነገረ ሃይማኖት ማዕከል ነገረ ድኅነት ነው። በአባ ጊዮርጊስም ድርሰቶች የምናየው ይህንኑ ነው። ከድርሳናቱ አንዱ በሆነው ውዳሴ መስቀል እንዲህ ይላል፡-
- ‹‹ብእውነትም የእግዚአብሔር ልጅ ሊገድሉት ይገባል፤ለሙታን ሕይወትን ይሰጣቸው ዘንድ በእውነትም የእግዚአብሔርን ልጅ ሊገድሉት ይገባል፤ በመስቀሉ ዓለምን ይቀድሳት ዘንድ ባይሰቀል ኖሮ ሕይወትን ባላገኘን ነበር። የእነርሱ /የአይሁድ/ ስህተት ለአህዛብ ሀብት ሆነ፤ ይሰቅሉትም ዘንድ ዕራቁቱን አደረጉት፤ መብራት በልብስ ሊሸፈን አይገባውምና፤ ለሚፈልጉት ሁሉ ብርሃኑን ያሳይ ዘንድ በማብሪያው ላይ ሊኖር ይገባዋል እንጅ ወደ መስቀል ላይ አወጡት፤ መብራት በምድር ላይ ሊቀመጥ አይገባውምና፤ በብርሃኑ ለሚመላለሱ ያበራላቸው ዘንድ ወደ መቅረዙ ሊወጣ ይገባዋል እንጅ። እርሱ ራሱ በወንጌል “መብራትን አብርተው በአልጋ ሥር አያደርጓትም ወይም በዕንቅብ አይሸፍኗትም፤ ነገር ግን ለሁሉ ታበራ ዘንድ በመቅረዝ ላይ ያስቀምጧታል” እንዳለ።

- “መቅረዝ የተባለውም መስቀል ነው፤ መብራት የተባለውም አማኑኤል ነው፤ እንግዲህ በወልደ እግዚአብሔር በብርሃኑ እንመላለስ፤ በእርሱ የሚያምን ሁሉ ወደ ብርሃን ይሔዳል፤ ጨለማ አያገኘውምና።...በመስቀል ስም በሰው ልጅ እንደበት ሊነገር የማይቻል ምሥጢር አለ፤ በመስቀል ስም የሰቃልያንን ማኅበር የሚበትን ምሥጢር አለ፤ በመስቀል ስም የእባቡን ራስ የሚቀጠቅጥ ምሥጢር አለ።” ይላል።

/ዳንኤል ክብረት (ዲ/ን)፣ ውዳሴ መስቀል፣2005 ዓ.ም ገጽ 70/

- በዚሁ መጽሐፍ /ውዳሴ መስቀል/ በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል፡-
- ‹‹አቤቱ ትኅትናህ ትዕቢተኞችን ጣላቸው፤ የመስቀልህም ኃይል ሲኦልን ደመሰሳት፤ በሞትህ ሙታን ሕያዋን ሆኑ፤ በትንሣኤህም ስቃዮችህ አፈሩ፤ በእጅህ ችንካር የጠላት ሆድ ተመታ፤ በመስቀልህ ጦር አውሬው ተወጋ፤ በመለኮትህ ሰይፍ የመልአከ ሞት ራሱ ተቆረጠ፤ በበትርህም ኃይል የእባቡ ራስ ተጠመደ፤ አንተ በመስቀልህ ትልቁን ዘንዶ አሰርከው፤ በጅራቱ የዓለምን ተራሮች ይስብ፣ ጽኑዓንንም ያሸንፍ ነበር፤ በቅንድቦቹ የዮርዳኖስን ወንዝ ይመጥጠው ነበር፤ አይፈስምም ነበር፤ ዓይኑን ከገለጠ በኋላ በሰባት ቀናት ይሰበሰብ ነበር፤ በፊቱም ማንም ችሎ መቆም አይችልም ነበር፤ አንተ ግን በመስቀልህ አዋረድከው ፤ / ወንዙንም/ መላኸው፤ አፍንጫውንም እንደ ወፍ አነቆርከው፤ በዚያም ላይ ቀለበት አደረግክበት፤ ለሲኦል ምርኮኞችም ታየሃቸው፤ ለገሃነም ጭፍሮችም ኀፍረትን አላበስካቸው።

- የሚያስለቅሱ የነበሩ አለቀሱ፤ እሪም አሉ፤ የሚያቄስሉትም ቆሰሉ፤ ያሳምሙ የነበሩ ታመሙ፤ ያለቀሱ ተደሰቱ፤ የተከዙም ፈነጠዙ፤ በመስቀልህ የታሠሩት ተፈቱ፤ ሕመምተኞችም ተፈወሱ፤ በመሰቀልህ የአዳም መርገም ተሻረ፤ ሔዋንም ነጻ ወጣች፤ በመስቀልህ የጨለማ ሰቅ ተሰነጠቀ፣ የብርሃንም ጌጥ ተሰፋ፤ በመስቀልህ የብረት ደጆች ተሰበሩ፤ የብረት መዝጊያዎችም ተቀጠቀጡ፤ በመስቀልህ የግነት በሮች ተከፈቱ፤ ዕረፍትም ተነጠፈ፤ በመስቀልህ የኦሪት ቃል ተፈጸመ፤ የትንቢቱ ቃልም ታተመ፤ በመስቀልህ የሰላም ዜና ተሰጠ፤ ሐዋርያትም አሕዛብን ለመጥራት ተላኩ፤ በመስቀልህ የመለኮት ወንጌል ተሰበከ፤ ምእመናንም አመኑ።››

/ዳንኤል ክብረት (ዲ/ን)፣ ውዳሴ መስቀል፣2005 ዓ.ም ገጽ 100/

የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የምሥጢራተ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ

- አባ ጊዮርጊስ ስለ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ብዙ ድንቅ ትምህርቶችን አስተምሯል። የምሥጢራተ ቤተክርስቲያንን አስፈላጊነት ብቻ ሳይሆን ከእነርሱ የሚገኘውን የእግዚአብሔር ጸጋም በሚያስደንቅ ሥዕላዊ አገላለጥ እንዲህ በማለት ይናገራል፦
- ‹‹የታመነች እናቴ እናታችሁም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በአብ ጥላ ሥር ታርፋለች፤ አቤቱ በጥላህ ውስጥ ማን ያርፋል? በመቅደስህም ማን ያድራል? ተብሎ እንደተጻፈ። ቀኙ ታቅፈኛለች፤ ግራውም ከራሴ በታች ነው ተብሎ እንደተጻፈ በሙሽራዋ እየተደሰተች በወልድ ክንድ ላይ ትደገፋለች። በመንፈስ ቅዱስ ብርሃን ፋናነት በግነት አጸዶች ውስጥ ትመራለች፤ ቅዱስ መንፈስህ በጽድቅ ጐዳና ይምራኝ የሚል እንደተጻፈ።
- ከዚያም በኋላ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም መጠመቅን ስትሻ ወደ ዮርዳኖስ ባሕር ወርዳ በመጠመቂያው ውስጥ ስለልጁ ምስክር በሆነ በእግዚአብሔር አብ ስም አንድ ጊዜ ትነከራለች። ሁለተኛም በዘካርያስ ልጅ በዮሐንስ እጅ በተጠመቀ በእግዚብሔር ወልድ ስም ትነከራለች፤ እንደገናም ከሰማያት ወርዶ በሥጋዊ ርግብ አምሳል በጌታ በኢየሱስ ላይ በተቀመጠ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስም ሦስተኛ ትነከራለች። ከዚያም ከዮርዳኖስ ውሃ ወጥታ የክርስቶስ ሴት አገልጋይ ትባል ዘንድ የሚሮን ቅባት ማኅተምም ትቀበላለች፤ የሚሮን ቅባት ሐዋርያት በዲዲስቅልያ እንደተናገሩት የሃይማኖት ኃይል ነው።...

- ከዚያም ነቢያት ሁላቸው በትንቢት አርጋኖን ስብከትን ወደሚያሰሙበት፣ የግሊላም ሕፃናት ጎሊናን በሚመስጥ፣ ልብን በሚስብ፣ አጥንትንም በሚያለመልም የምስጋና ቃል ወደሚያመሰግኑበት፣ ጴጥሮስ የመንግስተ ሰማያትን መክፈቻዎች ወደተቀበለበት፣ ጳውሎስም ለቤተክርስቲያን ብርሃን ሊሆን ወደተጠራበት፣ ዮሐንስ የመለኮትን ምሥጢር እየሰበከ እንደ ቀንደ መለከት ወደሚጮህበት፣ ሐዋርያትም ሁላቸው በመንፈስ ቅዱስ መውረድ የእሳትን ፈሳሽ ወደጠጡበት፣ የመላእክት ወገኖች የእግዚአብሔርን መሠዊያ ለመጐብኘት ወደሚተጉበት፣ የድካማቸውንና የመከራቸውን ዋጋ አክሊል የተቀዳጁ የደናግልና የመነኮሳት ወገኖች ወዳሉበት ወደ ሠርጉ ሥፍራ ትገባለች።
- ከዚያም በኋላ ለምእመናን ምሳ ሙሽራው በሙሽሪት አዳራሽ ይታረዳል። መታረዱን ከማየት የተነሣ ጉልበቷ ይንቀጠቀጣል፤ አንጀቷም ይናወጻል። በመሠዊያው ቀንድ ሲንጠፈጠፍ ደሙን ባየች ጊዜ ሥጋውን በፍርሃት ትበላለች፤ ደሙንም በመንቀጥቀጥ ትጠጣለች፤ ከዚያም የሃይማኖት ወላፈን በልቧ ውስጥ ይግላል፤ የፍቅሩም ሞገድ በሆዷ ውስጥ ይፈላል።››
- /መጽሐፉ ምስጢር የጥምቀት ምንባብ/

- በፋሲካ ጎሙስ በሚነበበው እና ለአርጌንስ መልስ በተሰጠበት ቦታም እንዲህ ይላል፡-
- “...የክርስቲያን ታናሽ የሆነውን የክርስቲያን ታላቅ ለመሆን በተጸለየበት የመጠመቂያ ውኃ ሲያጠምቁት ከቀደመ ኃጢአቱ ይነጻል፤ ሕዝቅኤል ጥሩ ውሃን ረጫችኋለሁ ትጠሩማላችሁ ብሎ ትንቢት እንደተናገረ። ከዚያም በኋላ የማክበሪያውን ቅባት ይቀቡታል፣ ይህውም የበለሳን ዘይት / ሜሮን/ ነው፤ ዳዊት ራሴን በዘይት ቀባኸኝ እንዳለ
- “እነሆ ማንጻት ቀደመ፤ መቀደስም ተከተለ። እንዲሁም ለምእምናን ራሳቸውን በንስሐ ማንጻት ሊያስቀድሙ ከዚያም በኋላ ቅዱሳን ይሆኑ ዘንድ የተቀደሰውን ምሥጢር /ሥጋ ወደሙን/ ሊቀበሉ ይገባቸዋል፤ ካህኑ ቅድሳት ለቅዱሳን እያለ ይከሰዋልና ። ይህም ማለት የምትቀበለው ሆይ ንጹህ ካልሆንህ ራስህን ዕወቅ እነሆ የንጹህንን ሥጋ ይቀድስ ዘንድ ነውር ነቀፋ የሌለበትን ንፁሁን በግ አርደዋለሁና፤ ስለዚህም ቅድሳት ለቅዱሳን ብዬ መስከርሁልህ ማለት ነው።”

- አባ ጊዮርጊስ አርጋኖን በተባለ የምሥጋና ድርሰቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ አያሌ ነገሮችን ተናግሯል። ለምሳሌ ያህል በሰኑይ አርጋኖን ምሥጋናው ምሥጢረ ቁርባንን በተመለከተ እንዲህ ይላል፡-
- ‹‹የንጽሕት እምቦሳ ልጅ የናዝሬቱ ኢየሱስ በእውነት ንጹሕ የተወደደ መሥዋዕት ነው። ለመታረድ የማያቋርጥ፣ እርዱ የማያልቅ፣ ንጹሕ ላህም፣ እውነተኛ መሥዋዕት ነው። የሚበሉትን የሚቀድሳቸው፣ የሚቀበሉትንም የተመሰገኑ የሚያደርጋቸው እርሱ እውነተኛ ንጹሕ መሥዋዕት ነው። በእሥራኤል እጅ የተሠዋ እርሱ እውነተኛ ንጹሕ መሥዋዕት ነው። በአይሁዳዊ እጅ የተሠዋ እርሱ እውነተኛ ንጹሕ መሥዋዕት ነው። በወጉት ሬት በቀንዱ የማይበረታታ ላም፣ በሚሸልቱትም ሬት የማይናገር በግ እውነተኛ ንጹሕ መሥዋዕት ነው። በፊቃዱ የታመመ፣ የሞተ እርሱ ንጹሕ መሥዋዕት ነው። ዘወትር የሚሠዋው፣ ዘወትርም ሕያው ሆኖ የሚኖረው የጎኑ መዳሰስም የማያልቀው እርሱ የእውነት መሥዋዕት ነው።››

/አርጋኖን ዘሰኑይ/

- በዚሁ የአርጋኖን ድርስቱ የምስጢረ ክህነትን ክብር እንዲህ በማለት ይገልጣል
- “ይህንን እሳት ያለጉጠት ሳይፈራ የሚዳስስ ካህን እንደምን ያለ ነው? ለዚህ ለመዳሰሱ አንክሮ ይገባል። በመሠዊያ ላይ ይህንን ጎብስቱን የሚፈትትው ካህን እንደምን ያለ ነው? ለዚህ ለመፈተቱ አንክሮ ይገባል። ብላቴናውን ባባቱ ፊት በእናቱ ራስ ላይ አኑሮ የሚሠዋ ይመስላል። የምሥጢሩን ወይን በጽዋው የሚያዘጋጀው ካህን እንደምን ያለ ነው? ለዚህ ለማዘጋጀቱ አንክሮ ይገባል የልጁን ደም በአባቱ ፊት ደሙንም በእናቱ ራስ ላይ ሲንጠፈጠፍ የሚቀዳ ይመስላል። ሙሽራውን ያለ ወቅለምት የሚሠዋ፣ ሙሽራይቱ የሙሽራውን ሥጋ እንድትበላ የሚጠራት፣ ልጆቿንም በአባታቸው ሥጋ የሚያሳድጋቸው ይህ ካህን እንደመን ያለ ነው? ለዚህ አንክሮ ይገባል። የእግዚአብሔርን በግ ለመሠዋት ጣቶቹ ወቅለምት የሆኑለት ይህ ካህን እንደምን ያለ ነው? ለዚህ አንክሮ ይገባል።”

/አርጋኖን ዘሰኑይ/

- በመጨረሻም “ኃይል ወደቤተ ክርስቲያን አይወርድም፤ ጎብስቱም ወደ ክርስቶስ ሥጋነት አይለወጥም፤ የወይኑ ጽዋም ደሙን ወደ መሆን አይለወጥም” ለሚሉ ሰዎች ስለ ምሥጢራት የተናገረውን በመጥቀስ ይህንን ርዕስ እንፈጽማለን፡-
- “እኛስ ከከሀዲዎች መነሳሳት የተነሳ እንዳትነዋወጥ ኃይል ቤተ ክርስቲያንን ይጠብቃታል እንላለን። የሚጠብቃት እርሱ ሲሆን ኃይልን ትሸከመዋለች፤ ኃይልን ትጎናጸፋለች፤ ኃይልንም ትታጠቃለች፤ ኃይልም ይከብባታል፤ የሠራዊት ጌታ ሠረገላ አድርጓታልና።... እንዲሁም ጎብስትና የወይን ጽዋ ካህኑ አቤቱ የጌታችንን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም እንዲያደርገው በዚህ ጎብስት ላይ በዚህም ጽዋ ላይ ቅዱሱን ኃይል ትልክ ዘንድ እንለምንሃለን፤ እንማልድሃለን ብሎ በጭኸ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ መውረድ የክርስቶስን ሥጋና ደም መሆን ይችላል። ያለመለያየት በአንድ አካል ሲኖር ሰውነት ወደ አምላክነት አምላክነትም ወደሰውነት እንዳልተለወጠ እንዲሁ ጎብስትና የወይን ደም የመለኮት ኃይል ሲወርድበት ከፊተኛው መልክ አይለወጥም።...
- “በማርያም ማኅፀን ፍጹም የሕይወት እንጀራ ተጸነሰ። ይኸውም ለተቀደሰች ምሥጢር የበረከት ፍሬ ሆኖ የተሰጠ ከአብርሃም ዘር የተገኘ ሥጋ ነው። ከባሕርይዋ ደምም በመንፈስ ቅዱስ መገኰንት የወይን ፍሬ አፈራ። በአብም በመጋረዱ ኃይል የሚናገር የወይን ደም የመለኮትም ሥጋ ጎብስት ተፀነሰ።
- “ስለዚህም መድኃኒታችን ከሰማየት የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ሥጋዬን የበላ የእኔን ሥጋ ስለበላ በሕይወት ይኖራል፤ ደሜንም የጠጣ ሞትን አይቀምስም አለ። ዳግመኛም አብ ሕያው እንደሆነ እኔም የአብ ልጅ ስለሆንሁ ሕያው ነኝ ሥጋዬንም የበላ የእኔን ሥጋ ስለበላ በሕይወት ይኖራል አለ። እንዲህ ያለውን ጸጋ አቃልለን እንደምን እንድናለን?”

/ መጽሐፉ ምሥጢር የፋሲካ ዓርብ ምንባብ/

የአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ የነገረ ማርያም አስተምህሮ

- አባ ጊዮርጊስ እንደ ሌሎቹ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን መምህራን ሁሉ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ያላትን ቦታ በጥልቀት አስተምሯል። በሌሎች ትምህርቶችም ቢሆን ከምሥጢሩ ጋር አገናዝቦ የድንግል ማርያምን ነገር ይናገራል። ለእመቤታችን ከነበረው ታላቅ ፍቅር የተነሣ ስለእርሷ ክብር የሚያወሱ እና ምሥጋናን የተመሉ ድርሰቶችን ደርሷል። ከእነዚህም መጽሐፈ አርጋኖን እና መጽሐፈ ሰዓታት ተጠቃሾች ናቸው።
- አባ ጊዮርጊስ እመቤታችን ባመሰገነበት የአርጋኖን ድርሰቱ እንዲህ ይላል፦
- “እንድ ሰዓት እንኳ የድንግልናዋ መዝጊያ ያልተከፈተ፣ ዘላለም ተዘግታ የምትኖር ደጅ ሆይ ሕዝቅኤል ያየት የምሥራቅ ደጅ፣ ከኃያላን ጌታ በቀር በውስጧ የገባ የለም። በመግባቱ በመውጣቱ አልተከፈተችም። የንጽሕና ፍሬ የምታፈራ ድንግል እና አበባ የምታብብ ነባቢት ገነት ሆይ እርሷን ለመትከል ውሃም ለማጠጣት የደከመ የለም። የመለኮት ምንጣፍ የተነጠፈባት ንጽሕት አዳራሽ ሆይ፣ የንጽሕና ሙሽራ ቤት ርኩሰት የሌለባት የመንፈስ ቅዱስ ሠርግ ቤት፣ ከዕሴይ ሥር የተገኘች የወይን ሐረግ፣ ከዳዊት ግንድ የበቀለች በትር፣ ከርሷም አበባ የወጣ ይኸውም የቅዱሳን መዓዛ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።...

- “ከማይታዩ ረቂቃን መላእክት ከነፋሳት ይልቅ ረቂቅ የሆነ የማይታይ፣ በባሕርይ የተሠወረ አካላዊ ቃል በርሷ የተገለጠ ንጽሕት ሰፊ የተድላ ደስታ መጋረጃ። ሥጋዋን ባይጋርድ ባልታየም ነበር፤ ከርሷም የትስብእትን ድርብ በፍታ ባይጐናጸፍ ባልተገለጠም ነበር።...ለአዳምና ለልጆቹ ቤዛ የሚሆነውን የሕይወት መድኃኒት መሥዋዕት የምትሸከም መሠዊያ። እመቤቴ ድንግል ሆይ በብዙ ማናፈያ ካናፉት ከመሥሪያ እሳት ይልቅ የፍቅርሽ እሳትነት በሰውነቴ አዳራሽ ይሟሟቃል፤ ይላላባል እኮን”

/አርጋኖን ዘረቡዕ

ማጠቃለያ

- ከላይ እያለፍን የጠቀስናቸው የአበው ትምህርቶች ከሰፊ ድርሰቶቻቸው በጣም ጥቂቶቹን ለማሳያ ያህል ነው።
- የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ የበለጠ ለመረዳት ግን መጻሕፍቶቻቸውን ጊዜ ወስዶ በማስተዋል መመርመር ይገባል።
- ነገር ግን የአበውን ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያን ቋሚ ዶግማ እና ሥርዓት መሠረት እያገናዘበ የማይመረምር የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ በሚገባ ለመረዳት ይቸገራል፤ ትምህርተ ሃይማኖትን ለማስተማር የበቃ ነው ማለትም ያስቸግራል።